የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ — ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 16
ADDIS ABABA – 26th December 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፶፱/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኦፔክ ዓለም አቀፍ የልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፫፻፲፯

## CONTENTS

Proclamation No. 59/1996
Opec Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project Ratification proclamation ........................ Page 317

### አዋጅ ቁጥር ፶፱/፲፱፻፹፱

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፲ ሚሊዮን (አሥር ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፮ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኦፔክ ዓለም አቀፍ የልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፶፱/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 59/1996

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Opec Fund for International Development stipulating that the Opec Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 10,000,000 USD (ten million United States Dollars) for financing the Addis Ababa Bole International Airport Project, was signed in Addis Ababa, on the 15th day of July, 1996;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 26th day of December, 1996;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Opec Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project Ratification Proclamation No. 59/1996."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 1·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፮ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር ፮፻፷ፒ የብድር ስምምነት ነው ።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲ ሚሊዮን (አሥር ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 660P signed in Addis Ababa, on the 15th day of July, 1996 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Opec Fund for International Development.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 10,000,000 USD (ten million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 26th day of December, 1996.

Done at Addis Ababa, this 26th day of December, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE